የእምነት አንቀጾች

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን

፩ በዘለአለማዊ አባት እግዚአብሔር፣ በልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ እናም በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን።

፪ በአዳም መተላለፍ ሳይሆን፣ ሰዎች በራሳቸው ኃጢአት እንደሚቀጡ እናምናለን።

፫ የወንጌሉን ህግጋትና ሰርዓቶችን በማክበር፣ የሰው ዘር ሁሉ በክርስቶስ የኃጢአት ክፍያ አማካይነት መዳን እንደሚችሉ እናምናለን።

፬ የወንጌሉ ቀዳሚ መሰረታዊ መርሆችና ሰርዓቶች፥ አንደኛ፣ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነት፤ ሁለተኛ፣ ንሰሐ መግባት፤ ሶስተኛ፣ ለኃጢአት ሰርየት በመጥለቅ መጠመቅ፤ አራተኛ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሰጦታ ለመሰጠት እጆችን መጫን እንደሆኑ እናምናለን።

፭ ሰው ወንጌሉን ለመሰበክና በወንጌሉ ሰርዓትም ለማገልገል በትንቢትና ሰልጣን ባላቸው ሰዎች እጆችን በመጫን በእግዚአብሔር መጠራት እንዳለበት እናምናለን።

፮ በጥንቷ ቤተክርስቲያን እንደነበረው አንድ አይነት ድርጅት፣ በሰምም በሐዋርያት፣ በነቢያት፣ በአገልጋዮች፣ በአስተማሪዎች፣ በወንጌል ሰባኪዎችና፣ በሌሎችም፣ እናምናለን።

፯ በልሳን ሰጦታ፣ በትንቢት፣ በራዕይ፣ በመገለጥ፣ በመፈወስ፣ ልሳንን በመተርጎም፣ እናም፤ በመሳሰሉት ሰጦታዎችም እናምናለን።

፰ በትክክል እስከተተረጎመ ድረስ፣ መፅሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እናምናለን፤ ደግሞም መፅሐፈ ሞርሞንም የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ እናምናለን።

፱ እግዚአብሔር እስካሁን በገለጣቸው ሁሉ፣ አሁንም በሚገልጣቸው ሁሉ እናምናለን፣ እናም የእግዚአብሔርን መንግስት በተመለከተ ወደፊትም እርሱ በሚገልጣቸው ታላቅና አስፈላጊ ነገሮችም እናምናለን።

፲ ስለእስራኤል መሰብሰብና ስለ አሰሩ ነገዶች ዳግሞ መመለስ፣ ፅዮንም (አዲሲቷ ኢየሩሳሌም) በአሜሪካ ክፍለ አህጉር እንደምትገነባ፣ ክርስቶስ እራሱም በምድር ላይ እንደሚነግስ፣ እናም ምድርም ታድሳ ገነታዊ ክብሯን እንደምትቀበልም እናምናለን።

፲፩ ሁሉን የሚገዛው እግዚአብሔርን ህሊናችን እንደሚመራን የማምለክ መብት እንዳለን እናረጋግጣለን፣ እናም ሁሉም ሰዎች እንዴትም፣ የትም፣ ወይም ምንም የፈለጉትን ምንም እንዲያመልኩ እንደዚህ አይነት መብት እንዳላቸውም እንቀበላለን።

፲፪ ለንጉሶች፣ ለፕሬዘደንቶች፣ ለገዢዎች፣ እናም ለዳኞች ታዛዦች በመሆን፣ ህግን በመታዘዝ፣ በማክበርና በመደገፍ እናምናለን።

፲፫ በታማኝነት፣ በእውነተኛነት፣ በንፅህና፣ በቸርነት፣ በምግባረ መልካምነት፣ እናም ለሁሉም ሰዎች በጎ ነገሮችን አድራጊ በመሆን እናምናለን፤ በርግጥም የጳውሎስን ምክርም እንከተላለን ለማለት እንችላለን—በሁሉም ነገሮች እናምናለን፣ በሁሉም ነገሮች ተስፋ እናደርጋለን፣ በብዙ ነገሮች ፀንተናል፣ እና በሁሉም ነገሮች መፅናት ስለመቻል ተስፋ አለን። ምግባረ መልካም፣ የሚያስደስት፣ ወይም መልካም ሀተታ ወይም ምሰጋና የሚገባው ምንም ነገር ቢኖር፣ እኛም እነዚህን እንሻለን።

ጆሴፍ ስሚዝ።

Unofficial poster layout of the text published on churchofjesuschrist.org. Not an official publication of The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints. Generated by Urim, urim.samuelbaird.com